# ቅንጅት ዓለም አቀፍ ሳዕላይ ምክር ቤት
## Kinijit International Council

ሐምሌ 20 ቀን 1999 ዓ.ም.

## አጭር መግለጫ

የቅንጅት ማዕከላዊ አመራር በውጭ የሚገኙትን የቅንጅት አካላት በተመለከተ ሐምሌ 20 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው መምሪያ ደርሶናል። መምሪያው ቀደም ሲል የቅንጅት አመራር ለወህኒ በመዳረጉ የፖለቲካ አመራሩን በሀላፊነት የሚመራ የቅንጅት ዓለም አቀፍ አመራር መሰየሙን አስታውሶ አሁን ግን የቅንጅት አመራር ከወህኒ በመውጣቱና መደበኛ ሥራውን የጀመረ በመሆኑ ቀደም ሲል ከስልጣኑ ቀንሶ በውክልና የሰጠውን የፖለቲካ አመራር ውክልና በማንሳት ራሱ እንደሚያካሄደው ገልጧል። ለቅንጅት የሚደረገው የድጋፍ ሰጪነት ተግባር በተመለከተ ግን የተጀመረው ሥራ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አሳስቧል።

የድጋፍ ሰጪነቱ ሥራ ይበልጥ ውጤታማ የሚሆንበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እንዲቻል ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር የሚመክርና ውሳኔ የሚሰጥ የከፍተኛ አመራሮች የልዑካን ቡድን በቅርብ ቀናት ወደ አሜሪካ እንደሚመጣም ተገልጧል።

ቅንጅት ዓለም አቀፍ ምክር ቤትም የድጋፍ መስጠቱ ሥራ በሠመረና በተቀናጀ መልኩ እንዲከናወን በሚደረገው ጥረት የተሰጠውን ሀላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ጥረቱን እንደሚቀጥል በዚህ አጋጣሚ ይገልጣል።

የቅንጅት ትግል ይሰምራል! !

የቅንጅት ዓለም አቀፍ ሳእላይ ምክር ቤት
ሐምሌ 20 ቀን 1999 ዓ.ም.